# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ሳምሶም፣ ጠንካራው የእግዚአብሔር ሰው፡፡


ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ከብዙ ጊዜአት በፊት ፣ በእስራኤል ምድር ፣ ማኑሔ የሚባል ሰው ይኖር ነበረ፡፡ እርሱና ሚስቱም ልጆች አልነበሯቸውም፡፡ አንድ ቀንም የጌታ መልአክ ለማኑሔ ሚስት ተገለጠላት፡፡ “እጅግ የተለየ ልጅ ይኖርሻል” ብሎ ነገራት፡፡



እርሷም አስደናቂውን ዜና ለባሏ ነገረችው፡፡ ማኑሔም ጸለየ ፤ "አ ጌታዬ…….. እንደገና ጎብኘን፡፡ ለልጁ ምን ማድረግ እንዳለብን አስተምረን አለው፡፡"



3

መልአኩም ለማኑሔ ልጁ ፀጉሩን መቆረጥ እንደሌለበት ፤ የሚያሰክር መጠጥ እንዳይጠጣና አንዳንድ ምግቦችን እንዳይመገብ ነገረው፡፡ እግዚአብሔር ይሔንን ልጅ ፈራጅ እንዲሆን መረጠው፡፡ እስራኤልንም ይመራል፡፡





4



የእግዚአብሔር ሕዝብ በእርግጥም ረዳት ያስፈልጋቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን ከሕይወታቸው ውስጥ አውጥተውት በፍልስጤማዊያን እጅ እየተሙቱ ነበረ፡፡ ነገር ግን ፤ ሲጸልዩ እግዚአብሔር ሰማቸው፡፡ የአለም ጠንካራው ሰው የሚሆነውን ይሄንንም ልጅ ላከላቸው፡፡

5

"ሴቲቱም ልጁን ወለደችና ስሙን ሳምሶም ብላ ጠራቸው፡፡ ልጁም አደገ ፤ እግዚአብሔርም ባረከው፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ ያርፍ ጀመር፡፡" ሳምሶምም እጅግ ጠንካራ ሆነ፡፡ አንድ ቀን ከደቦል አንበሳ ጋር ባዶ እጁን ታገለ ፤ ከዚያም አንበሳውን ገደለው፡፡



6



ከዚያም ፤ ሳምሶም በሞተው አንበሳ ውስጥ ከተገኘ ንቦች ከሰሩት ማር ወስዶ በላ፡፡ አንቆቅልሽም ተናገረ ፤ " ከበላተኛው ውስጥ ለመብል የሚሆን ወጣ እናም ከጠንካራው ውስጥም ጣፋጭ ነገር ወጣ" ማንም ትርጉሙን ሊገምት አልቻለም - ነገር ግን የሳምሶም አዲሷ ሚስት የሆነችው ፍልስጤማይቷ ለጓደኞቿ ነገረቻቸው፡፡ ይሄም ሳምሶምን እጅግ አበሳጨው፡፡

7

ፍልስጤማዊያን የሳምሶምን ሚስት ወስደው ለቅርብ ጓደኛው ሲሰጧት እጅግ ተበሳጨ፡፡ በቀል ለመፈጸም አቀደ፡፡ ነገር ግን ፤ እንዴት? ሳምሶም 300 ቀበሮዎችን ያዘ፡፡ ከዚያም ጭራቸውን በአንድ ላይ አሰረው ፤ ሁለት በ ሁለት አድርጎ የሚንበለበል እሳትን አደረገባቸው፡፡



8

ከዚያም ሳምሶም በፍልስጤማዊያን የሰብል እርሻ መካከል ለቀቃቸው፡፡



9

አሁን ፍልስጤማዊያን ሊበቀሉ አሰቡ፡፡ ሳምሶም ታሰሮላቸው
በፍልስጤማዊያን ሊገደል ተወሰደ፡፡



10

ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በሳምሶም
ላይ መጣ፡፡ ገመዶቹን በጣጠሰ ፤ ከሞተ
አህያ ውስጥ አዲስ መንጋጋ አንስቶ አንድ
ሺህ ጠላቶቹን ገደለ፡፡



11

ፍልስጤማዊያን ሳምሶምን የሚፈልጉ ቡድኖችን ፈለጉ፡፡ አንድ ምሽት ፤
በከተማው ውስጥ ያዙትና የከተማውን በር ዘጉት፡፡ ነገር ግን ሳምሶም
የከተማውን በር በትከሻው ላይ ተሸክሞት ከከተማው ተራምዶ ወጣ፡፡



12

ነገር ግን ሳምሶም እግዚአብሔርን በደለ፡፡
ሰምሶም የጥንካሬውን ምስጢር ቆንጆ
ለሆነችው ለፍልስጤማይቷ ሰላይ ለደሊላ
ነገራት፡፡ እርሷም ተኝቶ ሳለ የሳምሶምን
ጸጉር ላጨችው፡፡



13

ከዚያም ፍልስጤማዊያን ወታደሮች
ሳምሶምን በደሊላ መኝታ ክፍል
ውስጥ አግኝተውት አጠቁት፡፡
ሳመሶምም በሃይለኛው ተፋለማቸው
- ነገር ግን ጥንካሪው ከእርሱ ርቆ
ነበረ፡፡ ጠላቶቹም አይኑን አወጡት፡፡
አይነስውሩ እና ደካማው ሳምሶም
የፍልስጤማዊያን ባሪያ ሆኖ ቀረ፡፡
እነርሱም በእግዚአብሔር አግልጋይ
ላይ ይሱቀና ይሳለቁ ነበረ፡፡



14

ፍልስጤማዊያኑ በአል ነበራቸው፡፡ ሳምሶምን አሳልፎ ስለሰጣቸው የእነርሱን የውሃ ውስጥ አምላክ የሆነውን ዳጎንን አመሰገኑት፡፡ በዳጎን ቤተመቅደስ ውስጥ እየጠጡ ይደሰቱ ነበረ፡፡ ከዚያም ፣ ለእነርሱ እንዲጫወትላቸው ሳምሶምን ይጣሩት ነበረ፡፡



15

እንድ ትንሽ ልጅም ሳምሶምን ይዞት መጣ ፤ ቤተመቅደሱን ይዞ ወዳቆመው ምሶሶ እንዲጠጋ አደረገው፡፡ ከጣሪያው ስር ወደ ሶስት ሺህ የሚጠጉ ፍልስጤማዊያን ተሰብስበው ነበረ ፣ ብዙዎችም በመቅደስ ውስጥ ነበሩ ፤ ሁሉም ሲያፌዙበት ነበረ፡፡



16

በወህኒ ቤት ውስጥም ሆኖ የሳምሶም ጸጉሮች ያድግ ነበረ፡፡ እርሱም እንዲህ ሲል ጸለየ ፣ “ እባክህ አምላኬ አንድ ጊዜ አጠንክረኝና ስለሁለቱ አይኖቼ ስል ልበቀላቸው፡፡”



17

እግዚአብሔር ዳግም ለሳምሶም ኃይልን ሰጠው; ሳምሶም የማይቻለውን ማድረግ ተችሎታል? አዎ! አዎ! አጠንክሮ በመያዝና በመግፋት ፣ ሳምሶም ታላላቆቹን ምሶሶዎች ሰነጣጠቃቸው፡፡ የዳጎን መቅደስ ወድቆ ፈረካከሰ፡፡ ሳምሶምን ጨምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ፍልስጤማዊያንን ገደላቸው፡፡



18

ሳምሶም፣ ጠንካራው የእግዚአብሔር ሰው፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

መሳፍንት 13 -16

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

19




14

60

20

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16